## መመሪያ ቁጥር………/ 2015

## የፖሊክሎሪኔትድ ባይፌናይል ቁሶች እና በፖሊክሎሪኔትድ ባይፌናይል የተበከሉ ቁሶችን ከአገልግሎት ውጭ ለማድረግ የወጣ መመሪያ

የፖሊክሎሪኔትድ ባይፌናይል ቁሶች እና በፖሊክሎሪኔትድ ባይፌናይል የተበከሉ ቁሶችን አጠቃቀም በአካባቢ ደህንነት ላይ ሊያደረሱ የሚችለውን ተፅዕኖ ሊከላከሉ ወይም ሊያሳንሱ የሚችሉ መስፈርቶችን መደንገግ በማስፈለጉ፤

የፖሊክሎሪኔትድ ባይፌናይል ቁሶች እና በፖሊክሎሪኔትድ ባይፌናይል የተበከሉ ቁሶች በእጃቸው የሚገኙ ሰዎች ኬሚካሉን ሙሉ በሙሉ በሂደት ከአገልግሎት ውጭ እንዲያደርጉ እንዲሁም የሚያስወግዱበትን የጊዜ ሰሌዳ በግልፅ መደንገግ በማስፈለጉ፤

የፕላንና ልማት ሚኒስቴር በአስፈፃሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀፅ 19 (4) መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የፖሊክሎሪኔትድባይፌናይል ቁሶች እና በፖሊክሎሪኔትድ ባይፌናይል የተበከሉ ቁሶችን ከአገልግሎት ውጭ ማድረጊያ መመሪያ ቁጥር……/2015 "ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1. "ባለሥልጣን" ማለት የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ነው፤
2. "ፖሊክሎሪኔትድ ባይፌናይል" ማለት በባይፌናይል ሞለኪዩል ውስጥ ካሉት ቢያንስ ሁለቱ ሃይድሮጅን አቶሞች በክሎሪን አቶሞች በኬሚካላዊ መንገድ ሲተኩ የሚገኙ ተዛማጅነት ያላቸው በርካታ ኬሚካሎች ስብስብ ነው፤
3. "በፖሊክሎሪኔትድ ባይፌናይል የተበከለ ቁስ" ማለት ፈሳሽ ያልሆነ ቁሶ ሆኖ በውስጡ የያዘው የፖሊክሎሪኔትድ ባይፌናይል ክምችት መጠን 50ና ከ50 ፒ.ፒ.ኤም በላይ እና 500ና ከ500 ፒ.ፒ.ኤም በታች የሆነ፤ ወይም ፈሳሽ ቁስ ሆኖ

በውስጡ የያዘው የፖሊክሎሪኔትድ ባይፌናይል ክምችት መጠን 50ና ከ50 ፒፒኤም በላይ እና 500 እና ከ500 ፒ.ፒ.ኤም በታች የሆነ ቁስ ነው፤፤

4. "የፖሊክሎሪኔትድ ባይፌናይል ባለቤት" ማለት የፖሊክሎሪኔትድ ባይፌናይል ቁሳቁሶችን ወይም በፖሊክሎሪኔትድ ባይፌናይል የተበከለ ቁሳቁስ እና ቆሻሻ የሚጠቀም ወይም የሚያከማች ሰው ነው፤
5. “ፖሊክሎሪኔትድ ባይፌናይል ያለባቸው ነገሮች” ማለት ሆን ተብሎ ወይም ባለማወቅ 50 ፒፒኤም ወይም ከዚያ በላይ ፖሊክሎሪኔትድ ባይፌናይል የተያዘበት ወይም የፖሊክሎሪኔትድ ባይፌናይል ክፍል ያለበት ማንኛውም ቁስ ነው፤
6. "የፖሊክሎሪኔትድ ባይፌናይል ቆሻሻ" ማለት በአደገኛ ቆሻሻ አያያዝ እና አወጋገድ አዋጅ ቁጥር 1090/2010 አደገኛ ቆሻሻ ተብሎ የተወሰነ ቆሻሻ ነው።
7. "ሰው" ማለት ተፈጥሯዊ ሰው ወይም ሕጋዊ ሰውነት ያለው አካል ነው።
8. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ጾታ ይጨምራል

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ ፖሊክሎሪኔትድ ባይፌናይል እና የፖሊክሎሪኔትድ ባይፌናይል ቁሶች በሚያመርት፣ በሚያከፋፍል ፣በሚጠቀም፣ በሚሸጥ እና በሚያስወግድ ማንኛውም ሰው ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

## 4. ክልከላ

ማኛውም ሰው ፖሊክሎሪኔትድ ባይፌናይል ቁስ እና በፖሊክሎሪኔትድ ባይፌናይል የተበከለ ቁስ ማምረት ፣ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት እና ወደ ውጭ ሀገር መላክ አይችልም።

## 5. የአገልግሎት ገደብ የጊዜ ሰሌዳ

1. ማንኛዉም ሰዉ እ.አ.አ ከ 2023 በኋላ ፖሊክሎሪኔትድ ባይፌናይልን ወይም በፖሊክሎሪኔትድ ባይፌናይል የተበከለ ቁስን ወይም የፖሊክሎሪኔትድ ባይፌናይል ቆሻሻን መጠቀም አይችልም።
2. የፖሊክሎሪኔትድ ባይፌናይል ቆሻሻን ለማስወገድ ካልሆነ በስተቀር ማንኛዉም ሰዉ እ.አ.አ ከ2026 በኋላ ፖሊክሎሪኔትድ ባይፌናይልን ፣በፖሊክሎሪኔትድ ባይፌናይል የተበከለ ቁስን ወይም የፖሊክሎሪኔትድ ባይፌናይል ቆሻሻን ይዞ መገኘት አይችልም።

## 6. ምዝገባ

1. ፖሊክሎሪኔትድ ባይፌናይልን ወይም በፖሊክሎሪኔትድ ባይፌናይል የተበከለ ቁስን ወይም የፖሊክሎሪኔትድ ባይፌናይል ቆሻሻን የያዘ ሰው ይህ መመሪያ በስራ ላይ በዋለ በዘጠና ቀናት ዉስጥ በባለሥልጣኑ ቀርቦ መመዝገብ አለበት፡፡
2. ባለሥልጠኑ የምዝገባ ማመልከቻ በተቀበለ በሰላሳ ቀናት ዉስጥ መመዝገብ አለበት፡፡
3. ባለሥልጣኑ የምዝገባ ማመልከቻ ሲደርሰዉ ተጨማሪ የጽሁፍ መረጃ እንዲቀርብ ወይም ማመልከቻዉ እንዲሻሻልና በቀጣይ አስራ አምስት ቀናት ዉስጥ እንዲቀርብ ማዘዝ ይችላል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የተመዘገበ ሰዉ በምዝገባዉ ዝርዝር ፍሬ ነገር ላይ ማንኛዉንም ለዉጥ ካደረገ በሰላሳ ቀናት ዉስጥ ለባለሥልጣኑ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

## 7. ፖሊክሎሪኔትድ ባይፌናይል ቁስ እና በፖሊክሎሪኔትድ ባይፌናይል የተበከለ ቁስ የአገልግሎት ጊዜ ገደብ እቅድ እና ቆጠራ

1. ማንኛውም የፖሊክሎሪኔትድ ባይፌናይል ቁስ እና በፖሊክሎሪኔትድ ባይፌናይል የተበከለ ቁስ የያዘ በባለሥልጣኑ የተመዘገበ ሰው ይህ መመሪያ በወጣ በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ የአገልግሎት ጊዜ ገደብ እቅድ በማዘጋጀት ለባለሥልጣኑ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ የአገልግሎት ጊዜ ገደብ እቅዱ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መረጃ መያዝ ይኖርበታል፡-

1)ስም እና አድራሻ፤

2)በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 መሠረት በባለሥልጠኑ የተሰጠ የምዝገባ ቁጥር፤

3) ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መረጃ የያዘ ጥቅም ላይ ወይም ክምችት ላይ የሚገኙ ፖሊክሎሪኔትድ ባይፌናይል ያልሆኑ ቁሳቁሶች፣ የፖሊክሎሪኔትድ ባይፌናይል ቁሳቁሶች እና በፖሊክሎሪኔትድ ባይፌናይል የተበከሉ ቁሳቁሶች አጠቃለይ ቆጠራ፤

ሀ) የዕቃው ዓይነት፣

ለ) መለያ ቁጥር፣

ሐ) የሚገኝበት ቦታ በጂ አይ ኤስ ኮኦርዲኔት የተመላከተ፣

መ) የአምራቹ ስም ፣

ሠ) የተመረተበት ቀን፣

ረ) የዳይኤላክትሪክ ፈሳሽ ይዘት ዓይነት፣

ሸ) የፈሳሽ ክብደት በ (ኪግ) ወይም የፈሳሹ መጠን (በሊትር)

ቀ) የፖሊክሎሪኔትድ ባይፌናይል ክምችት በፓርትስ ፐር ሚሊየን።

3. ማንኛውም ሰው ሁሉንም የፖሊክሎሪኔትድ ባይፌናይል ቁሳቁስ ወይም በፖሊክሎሪኔትድ ባይፌናይል የተበከለ ቁሳቁስ አገልግሎት ላይ ለማዋል የሚያቀርበው የአገልግሎት ጊዜ ገደብ እቅድ በዚህ መመሪያ አንቀፅ አምስት ላይ ከተቀመጠው የጊዜ ገደብ መብለጥ የለበትም።

4. ባለሥልጣኑ የአገልግሎት ጊዜ ገደብ እቅዱን በተቀበለ በሀያ የስራ ቀናት ውስጥ የመጨረሻ ውሳኔ መስጠትና ይህንንም ለአመልካች በፅሁፍ ማሳወቅ አለበት።

5. ባለሥልጣኑ እንደአስፈላጊነቱ አመልካቹን በ 15 ቀናት ውስጥ ተጨማሪ መረጃ እንዲያቀርብ ወይም እንዲያሻሽል ሊጠይቅ ይችላል።

6. በባለሥልጣኑ የአገልግሎት የጊዜ ገደቡ የፀደቀለት ሰው እቅዱን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው በቅድሚያ ለባለሥልጣኑ ማሳወቅ አለበት።

8. ሪፖርት

1. ማንኛውም ፖሊክሎሪኔትድ ባይፌናይል የያዘ ሰው በአመት ሁለት ጊዜ በኦዲተሮች የተዘጋጀውን ዘገባ የፀደቀው የአገልግሎት ጊዜ ገደብ እቅድ ጊዜ ከማለፉ በፊት በራሱ ወጪ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት።

2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 የተጠቀሰው የኦዲት ዘገባ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት መረጃ መያዝ ይኖርበታል፡-

ሀ. የኦዲተሩ አጭር ግለ ታሪክ መግለጫ ፤

ለ. ፖሊክሎሪኔትድ ባይፌናይል ያያዘ ሰው ወይም ዘገባውን የሚያቀረበቀው ሰው ስምና አድራሻ

ሐ. በባለሥልጣኑ የፀደቀ በሂደት ከአገልግሎት ውጭ ለማድረግ የተዘጋጀ ዕቅድ አተገባበር ዘገባ፤

መ. በባለሥልጣኑ የተሠጠ ደህንነቱ የጠበቀ የፖሊክሎሪኔትድ ባይፌናይል ቆሻሻ አወጋገድ የምስክር ወረቀት ቅጂዎች፤

ሠ. በዚህ መመሪያ መሰረት ከብክለት እንዲፀዱ ተደርገው ወደ አገልግሎት የተመለሱ ቁሳቁሶች የቤተ-ሙከራ ስራ ውጤት፤

## 9. መመሪያው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በፍትሕ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በተቋሙ ድረ ገጽ ላይ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡